# የኮቪድ-19 ክትባቶች ክሊኒካዊ ሙከራ በነማን ላይ ተካደ?

**አፕሪል 14, 2021**

ማንኛውም ክትባት በጥቅም ላይ ለመዋል ከመፈቀዱ በፊት ስኬታማና ደኅንነቱን የጠበቀ መሆኑን ለማረጋገጥ በበርካታ ግለሰቦች ላይ የሙከራ ጥናት ይከናወናል። ይህ ክሊኒካል ሙከራ በመባል ይታወቃል። የኮቪድ-19 ክትባቶች የምርት ሂደት ውስጥ የተሳተፉት ሳይንቲስቶች በተለያዩ ዜጋዎችን እና የማኅበረሰብ አባላት ላይ ያከተተ ጥናት አካሂደዋል።

## የክትባቶቹ ጥናት እና ሙከራ በተለያዩ ዜጎችና ማኅበረሰቦች ላይ ለምን ተካሄደ?

ማንኛውም የክትባት ምርት የተለያዩ ሕዝቦችን በበጎ ፈቃደኝነት የሚያሳተፍ ሂደት ሊኖረው የተገባ ነው። በኮቪድ-19 ክትባቶች መመረት ላይ የተሳተፉ ሳይንቲስቶች በወረርሽኙ በከፍተኛ ደረጃ የተጠቁት እና ለሞትም የተዳረጉት የነጩ ማኅበረሰብ አባላት ያልሆኑት እንደሆኑ በማወቃቸው በተለይም እነዚህን በከፍተኛ ደረጃ የተጠቁትን የማኅበረሰብ ክፍሎች በጥናቱ እና በሙከራው እንዲሳተፉ የተለየ ትኩረትና ጥረት አድርገዋል። ይህም ሂደት ሁሉም ሰው ከወረርሽኙ እንዲጠበቅ ለማድረግ ይረዳል።

## በሙከራ ጥናት ውስጥ የተሳተፉት ግለሰቦች ምን ያህሉ ከተለያዩ ማኅበረሰብ ነበሩ?

በካናዳ በጥቅም ላይ እንዲውሉ የተፈቀዱት የኮቪድ-19 ክትባቶች በሺህ የሚቆጠሩ ከተለያዩ ማኅበረሰብ በተወጣጡ ዜጎች ላይ ሙከራ ተደርጎባቸዋል። ከዚህ በታች የሚገኘው ሰንጠረዥ ዝርዝሩን ያመለክተናል።

| የተለያዩት ማኅበረሰብ / ዜጋ (በራስ ገለጻ መሠረት)* | የሞደርና ክትባት | የፋይዘር -ባዮንቴክ ክትባት | ጆንሰን እና ጆንሰን ክትባት | የአስትራ ዜኔካ ክትባት |
|---|---|---|---|---|
| ነጭ | 79% | 83% | 62% | 79% |
| ጥቁር / ጥቁር አሜሪካዊ | 10% | 9% | 17% | 8% |
| የእስያ ዝርያ | 5% | 4% | 4% | 4% |
| ኢንዲጂነስ (አሜሪካን ኢንዲያን/ አላስካ ኔቲቭ) | 0.8% | 0.5% | 8% | 4% |
| የሃዋይ ወይም የፓሲፊክ ደሴት ትውልድ | 0.2% | 0.2% | 0.3% | -- |
| ቅይጥ ዝርያ | 2% | 2% | 45% | -- |
| ሂስፓኒክ /ላቲን | 21% | 28% | 45.% | 22% |
| ሌላ | 2% | -- | 5% | -- |
| ያልታወቀ | 0.9% | 0.6% | 3% | -- |

*በጥናቱ ላይ የዋለው መስፈርት ከላይ የተመለከተውን ይመስላል። አንዳንድ ግለሰቦች ከአንድ በላይ መስፈርት የመረጡም አሉ።*



የሞደርና ክትባት የሙከራ ጥናት የተካሄደው በአሜሪካ ነው። የፋይዘር ባዮንቴክ ክትባት ጥናት በአሜሪካ፣ አርጄንቲና፣ ብራዚል፣ ጀርመን፣ ደቡብ አፍሪካ እና ቱርክ አገሮች ላይ ተካሂዷል።

የጆንሰን እና ጆንሰን ጥናት በአሜሪካ፣ ብራዚል፣ ደቡብ አፍሪካ እና እንደዚሁም በአምስት የላቲን አሜሪካ አገሮች ላይ ተካሂዷል። (እነዚህም አገሮች - አርጄቲና፣ ቺሊ፣ ኮሎምቢያ፣ ፔሩና ሜክሲኮ ናቸው)።

የአስትራዜኔካ ጥናት በአሜሪካ በ88 የተለያዩ ማዕከሎችና በፔሩና በቺሊ ተካሂዷል።

## ክትባቶቹ በተለያዩት ማኅበረሰቦች/ዜጎች ላይ ያሳየው ልዩነት አለ ወይ?

የሙከራው ጥናት በሁሉም  ላይ በስኬታማ ሁኔታ ከኮቪድ-19 በሽታ እንደሚከላከል ለማረጋገጥ ችሏል። በተለያዩት ማኅበረሰቦች/ዜጎች ላይ እኩል ስኬታማ ውጤት አሳይተዋል።

እስከ አፕሪል 14 ድረስ በዓለማችን እነ ቻይናን, ባንግላዴሽን እና ደብብ አፍሪካን ጨምሮ ሁሉንም ዓይነት ክትባቶች ያካተቱ ዶዞች ለ825 ሚሊዮን  ተሰጥተዋል። በክትባቶቹ ደኅንነት ላይ ይህ ነው የሚባል ከፍተኛ ችግር አልታየም።



ይህንን መረጃ ጠቃሚ ሆኖ እንደሚያገኙት ተስፋ እናደርጋለን። ለሌሎች ሼር በማድረግ እንዲያዳርሱት እንጠይቆታለን። መልክቱን በቪዲዮ ቀርጸውም ሊያስተላልፉት እንደዚሁም በሌላ ቋንቋ ተርጉመው ማስተላለፍ ይችላሉ።

ይህንን በሚያደርጉበት ጊዜ ይህንን መረጃ ያዘጋጁትን አካላት እንደ ምንጭ አድርገው መጥቀስ አይርሱ። እነዚህም ውመንስ ኮሌጅ ሆስፒታል (Women's College Hospital)፣ አካሲ (OCASI) ፣ ታይቡ የጤና ማዕከል (TAIBU Community Health Centre) እና ሬፉጂ 613 (Refugee 613) ናቸው።

አፕሪል 14 2021 በተጻፈበት ጊዜ ትክክለኛነቱ የተረጋገጠ

**በዚህ ጽሑፍ ውስጥ ያለው መረጃ በሚከተሉት የካናዳ ሐኪሞች ተረጋግጧል - ሜብ ራሺድ MD, የቶሮንቶ ዩኒቨርሲቲ, ረዳት ፕሮፌሰር, ቫኔሳ ሬዲት, MD, የቶሮንቶ ዩኒቨርሲቲ, ሌክቸር, እና አይዛክ አይ. ቦጎች, MD, የቶሮንቶ ዩኒቨርሲቲ, ተባባሪ ፕሮፌሰር**